# አስትሮ ኮሚክ

በ ሚሼል ዴኮኒንክ ትርጉም አምኃ  አድማሱ

## የወርቃማው ጅራታም ኮከብ ምስጢር

ሰኔ 2012

ወደ ቬርደን የተፈጥሮ ፓርክ

የኮሜት ሲ/2020 ኤፍ3 (NEOWISE) ጉዞ ምልከታ










በሚቀጥለው ቀን በተመሳሰይ በታ ላይ ፣ ግን እዚህ የበለጠ የጥበብ ሰው ከመሆን ይልቅ የተመራማሪ ሚናን መጫወት  እፈልጋለሁ። እንደ ጅራቱ ሁሉ በጅራታሙ ኮከብ ሐሰተኛ-እምብርት ውስጥ አንዳንድ ነገሮችን በዝርዝር አየሁ። በመደበኛ ባለ ጥንድ አጉሊ መነጽር እና የእኔ ተመራጭ በሆነው ባለ 5 ኢንች ቢኖ ቪክስሰን፣ ብዙ ማጉላትን እጠቀማለሁ። እኔም በንቃት የምሳተፍበት የICQ ዳታቤዝ (*) በሚጠበቀው መረጃ ላይ ትኩረቴን አደረግሁ፡ የመጠን ግምት፣ የጥዜት መጠን፣ የኮማ መጠን፣ የጅራቱ ርዝመት እና አቅጣጫው። (*) ICQ ኢንተርናሽናል ኮሜት ሦስት ወራዊ

የ "V"  ቅርጽ የሚሰራው ጅራቱ ምናልባትም ከፍተኛ የሆነ የአቧራ ምርትን ይጠቁማል።







ሰኔ 28 ፤ የቫለንሶል አምባ, በላቬንደር መዓዛ
የእይታዬን አቅጣጫዬን ለመቀየር፣ የምልከታ ቦታዬን ለመለወጥ እፈልጋለሁ።
ስጦታ ይመስል፣ ከኮማው ከጅራቱ በፊት ጠለቀ።
ሰኔ 30 ፤ በ ሳንቴ ኳ ሐይቅ ዳርቻ።
ሐምሌ 2 ከጠዋቱ 4 ሰአት ላይ፣ በህዋ ፊት ብቻዬን ያለሁ ያህል ተሰማኝ።
የዛን ቀን፣ የክዋክብት አናላይዘር ኔትወርክ ማጣሪያ የሶዲየም አቶም ቢጫ ልቀትን እንድመለከት አስቻለኝ።
አንጸባራቂ ቢጫ ቀለም ይህን ያማረ ወርቃማ ቀለም ለጅራታም ኮከቡ ሰጥቶታል።










የመጠን ግምቶችን የምሠራው ከዚህ ዓይነቱ ሥዕል በመነሳትነው። ክዋክብቱ እንደ መመዘኛ ሆነው ያገለግላሉ። ትክክለኛውን ልኬት ለመሞከር ዋናው ክዋክብቱን በጥንቃቄ የማስቀመጥ ጉዳይ ነው።




ሐምሌ 14
ይህ ክፍለ ጊዜ የቴክኒካዊ ብቻ መሆን ነበረበት ይሁን እንጂ በደመና መካከል የሚከሰት መብረቅ እና ፐርሴይድ በመሬት ገጽታ ላይ ተለዋዋጭነትን ጨምሯል።


የአዮን ጅራት ከአሁን በኋላ አይታይም ነገር ግን የአቧራ ጅራት  በጣም ረጅም ሆኖ ይታያል።
ቢኖ ቪክስን126 ሚሜ 40x


እንዲህ ዓይነቱ ንድፍ የኮማውን አክዘንግ ለመገምገም ያስችላል: 70,000 ኪ.ሜ, ከጁፒተር አክዘን ጋር የተቀራረበ።


ከምድር ላይ ሙሉውን የጅራት ርዝመት ከሞላ ጎደል ማየት እንችላለን።
ሐምሌ 16
የኒዮዋይዝ(NEOWISE) መመርመሪያ ይህንን ጅራታም ኮከብ  አገኘው እናም የእምብርቱ መጠን 5 ኪ.ሜ. ሆኖ አገኘው። ይህ ለጅራታም ኮከብ ትልቅ ነው!


የጅራቱን ርዝመት ለመገመት ቀላል ንድፍ መጠቀም ይቻላል።
0.7 UA
0.24 UA
20°
20 ° በመውሰድ ፤ ይህ የምድር-ቬነስ ሊኖር ከሚችለው ትንሹ ርቀት ይበልጣል።


ሐምሌ 17 ። አምስት በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ የሚገኙ ልጃገረዶች ተቀላቀሉኝ።
ምን ያህል ውብ እንደሆነ ተመልከቱ!


ከቬርደን ገደል በላይ፣ ከሴንት-ሎረንት መንደር ጋር ትይዩ።
በመኪናው ኮፈን ላይ ጅራታሙን ኮከብ እየሳልኩ ሳለ ጃኒክ ፎቶግራፍ አነሳችኝ። በእኛ ወርክሾፕ ውስጥ ይህን የውሃ ቀለም ለመሥራት ፎቶዋን ወሰድኩ… አሸናፊ ቡድን!
እናስ ኒዮዋይዝን (NEOWISE) አይተዋል? አይ ? እይዘኑ! የሚቀጥለው የጅራታሙ ኮከብ ጉብኝት  ለ8965 ዓ.ም ብቻ የታቀደ ነው።